

AskMCPS

ከሰዎች ጋር ማገናኘት፣ መልሶችንና የሚፈልጉትን እርዳታ መስጠት

በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች እና መልሶች

በትምህርት ቤት የልጄን የትምህርት እድገት እንዴት መከታተል እችላለሁ?

» የልጅዎን ውጤቶች፣ ትምህርት ላይ መገኘትን፣ የትምህርት አይነቶችን እና የሪፖርት ካርዶችን ለማግኘት "ParentVue" ይመዝገቡ። እንዲሁም ለተለያዩ አይነት ስፖርቶች መመዝገብ፣ ትምህርት ቤት መመዝገብ/ማስመዝገብ እና ከአስተማሪዎች መልእክት ለማግኘት እና ለመላክ ሊጠቀሙበት ይችላሉ። የእርስዎን "ParentVue" አካውንት ለመፍጠር ይህንን በይነመረብ ይክፈቱ፡- www.montgomeryschoolsmd.org/parents/tech-info-support

» MCPS ትምህርት ቤቶች፣ ከመምህራን፣ ከተማሪዎች፣ እና ከወላጆች ጋር ለመገናኘት እና መልእክቶችን ለመለዋወጥ፣ ParentSquare app ላይ ለመመዝገብ: ParentSquare Sign In ላይ ይመዝገቡ።

» ከትምህርት ቤትዎ መልዕክቶችን ለመቀበል እና ለመላክ "REMIND" መተግበሪያ እንዲኖሮት ይመዝገቡ። በማንኛውም ቋንቋ ይሰራል። መመሪያ ለማግኘት ይህንን በይነመረብ ከፍተው ይመልከቱ ፡- https://drive.google.com/file/d/17DzhkQZ8gA8n1OjfdygBArUXStoCI6RK/view

ልጄን እንዴት ትምህርት ቤት ማስመዝገብ እችላለሁ?

» ይህንን በይነመረብ ይክፈቱ፡- mcpsmd.org/enroll

» ሠነዶችን አባሪ አድርገው/(አያይዘው) ያቅርቡ

  » የነዋሪነት ማረጋገጫ (የኪራይ ውል ወይም የማብራት፣ ውኃ፣የመሳሰሉት የፍጆታ ክፍያ ሠነዶች)

  » የክትባት ማስረጃዎች

  » የተማሪ ፓስፖርት ወይም የልደት ቀን ማረጋገጫ ሠርተፊኬት

  » ፎቶግራፍ ያለበት የወላጅ መታወቂያ

» ቅጹን (ፎርሙን) ያስተላልፉ እና ማረጋገጫ ይሰጥዎታል

የልጄን ት/ቤት የአውቶቡስ መስመር እንዴት ማወቅ እችላለሁ? አውቶቡሱ ካልደረሰ ማነጋገር ያለብኝ ማንን ነው?

1. በዚህ በይነመረብ ላይ ይመልከቱ፡- MCPS Bus Route Locator: www.montgomeryschoolsmd.org/departments/transportation/busroutes/
2. ትምህርት ቤትዎን ይምረጡ እና ለእርስዎ የሚቀርበውን የአውቶቡስ ማቆሚያ ይፈልጉ!
   » ያገኛሉ
   » የአውቶቡስ ቁጥር
   » የሚቆምበት ቦታ
   » የሚወስድበት/የመቀበያ/ ሠዓት
3. አውቶቡሱ ካልደረሰ፣ የትራንስፖርት መምሪያን በስልክ ቁጥር 240-740-6200 ማነጋገር ይችላሉ።

ለተለያዩ ስፖርቶች ማስመዝገብ የምችለው እንዴት ነው?

1. "ParentVUE" ይክፈቱ
2. አንላይን ለማስመዝገብ "Athletics" የሚለውን ይምረጡ
3. ሠነዶችን ይጫኑ እና አያይዘው ያቅርቡ
   » የተሞላ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት አትሌቲክስ የቅድመ-ተሳትፎ ቅጽ
4. ያቅርቡ እና ከአትሌቲክስ ጽ/ቤት ማረጋገጫ እስኪያገኙ ይጠብቁ።

ትምህርት ቤት ለመማር ምን ዓይነት የጤና ማረጋገጫ ማስረጃዎች/ቅጾች ያስፈልጋሉ?

የተማሪው(ዋ) የክፍል ደረጃ፣ ለ MCPS አዲስ ከሆነ(ች)፣ እና በስፖርት እንቅስቃሴዎች ላይ ለመሳተፍ መቻል ወይም አለመቻል ይወሰናል። በጣም አስፈላጊ የሆኑ ቅጾች/ሠነዶች ከዚህ በታች ያሉት ናቸው፡-

ሁሉም ተማሪዎች

» ሁሉም ተማሪዎች አዲስ በሚመዘገቡበት ጊዜ እና ተማሪዎች አዲስ ክትባቶችን ሲወስዱ የሜሪላንድ የጤና ክትባት ሰርተፍኬት ያስፈልጋል። Mdh_896_form

ቅድመ-መዋእለ ህጻናት፣ መዋዕለ ህጻናት፣ ወይም 1ኛ ክፍል ምዝገባ ሲያደርጉ

» የሜሪላንድ የጤና ጥበቃ መምሪያ የደም ሊድ ምርመራ ሰርተፍኬት እንግሊዝኛ እና ስፓንሽኛ።

» የጤና መስፈርት ቅጽ በቅድመ መዋዕለ ሕጻናት ወይም በሄድ ስታርት ፕሮግራሞች ውስጥ ላሉ ተማሪዎች ሁሉ ያስፈልጋል። MCPS 567-1

አዲስ ተማሪዎች የአካል እና የጥርስ ምርመራ ያስፈልጋቸዋል።

» ወደ ሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) አዲስ ለሚገቡ ተማሪዎች የጤና ወይም የአካል ብቃት ምርመራ ያስፈልጋል። ለስድስተኛ ክፍል ተማሪዎችም እንዲሁ በወቅቱ የተደረገ ቅጽ ተሞልቶ መቅረብ አለበት። SR-6 የጤና ምርመራ ቅጽ

» ለአዲስ ተማሪዎች የጥርስ ጤና ምርመራ ቅጽ MCPS 525-17 ተሞልቶ እንዲያቀርብ ይመከራል።

በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ስፖርት ላይ የሚሳተፉ ተማሪዎች።

» ተማሪዎች በማንኛውም የትምህርት ቤት ስፖርቶች ከመሳተፋቸው በፊት የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት አትሌቲክስ ቅድመ-ተሳትፎ ቅጽ ሞልተው ማቅረብ አለባቸው።

ልጄ በትምህርት ቤት መድሃኒት መውሰድ ወይም ህክምና የሚያስፈልገው/የሚያስፈልጋት ቢሆንስ?

» የታዘዘለ(ላ)ትን መድኃኒት እና እንዴት እንደሚወሰድ ማስረጃ ቅጾችን ለትምህርት ቤትዎ የጤና ክፍል ያቅርቡ። እነዚህ ቅጾች MCPS የጤና አገልግሎት ድረ ገጽ ላይ ይገኛሉ፡- Health Forms - MCPS

ይበልጥ ዝርዝር መረጃ እና የጤና ምርመራ ቅጽ ለማግኘት ይህን በይነመረብ ይጎብኙ፡- www.montgomeryschoolsmd.org/departments/studentservices/mentalhealth/school-health-services

ልጄ የልዩ ትምህርት አገልግሎት የሚያስፈልገው/የሚያስፈልጋት ከሆነ እንዴት ድጋፍ ማግኘት እችላለሁ?

ስብሰባ እንዲዘጋጅ የልጅዎን ትምህርት ቤት ካውንስለር/አማካሪ ያነጋግሩ። ካውንስለሩ(ሯ) በግላዊ ሁኔታ የተዘጋጀ ትምህርት ፕሮግራም (IEP) የስብሰባ ሂደት ያስጀምራል/ታስጀምራለች። ይህ ስብሰባ ለልጅዎ የሚያስፈልገውን ድጋፍ ለመወሰን ይረዳል። ስለ ስፔሻል ኢጁኬሽን/ልዩ ትምህርት እዚህ ድረገጽ ላይ ይበልጥ ግንዛቤ ማግኘት ይችላሉ፦ www.montgomeryschoolsmd.org/departments/special-education/common-questions/overview/#overview1.

ልጄ የሚጠቀምበት/የምትጠቀምበት ቴክኖሎጂ በትክክል የማይሰራ ከሆነ ወይም ParentVUE ላይ እንዴት እርዳታ ማግኘት እችላለሁ?

ይህን ድረገጽ ይጎብኙ፦ montgomery.service-now.com/csm ወይም communitytechsupport@mcpsmd.org ኢሜል ያድርጉ።

መመሪያዎችን፣ ቪዲዮዎችን፣ ለማግኘት ወይም ለጥያቄዎችዎ ቨርቹዋል መልስ ለማግኘት ይህንን ገጽ መጠቀም ይችላሉ። ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት ይህንን ገጽ መጠቀም ይችላሉ።

MCPS ጉግል የይለፍ ቃል ብረሳውስ እንዴት ዳግመኛ ማግኘት እችላለሁ?

MCPS የራስ አገልግሎት የይለፍ ቃል ዳግም ማስተካከያ (SSPR) ይጠቀማል፦

1. ወደዚህ ድረገጽ ይሂዱ፦ sspr.mcpsmd.org
2. የእርስዎን MCPS ኢሜል ያስገቡ ለምሳሌ፦ (e.g., john.doe@mcpsmd.net)
3. እንደገና ማስተካከያ ይምረጡ፦ ኢሜይል፣ ቴክስት ጽሑፍ፣ ወይም የማረጋገጫ ጥያቄዎች።
4. የይለፍ ቃልዎን እንደገና ለማስጀመር የሚቀርቡትን ጥያቄዎች ይመልሱ።
5. ይሄ ካልሰራ፣ የልጅዎን ትምህርት ቤት ያነጋግሩ።

የኢሚግሬሽን ወኪል ወደ ትምህርት ቤቱ ቢመጣ ምን ይከሰታል?

- ትምህርት ቤቶቻችን፦ የማንኛውም ልጅ—የስደተኝነት/የኢሚግሬሽን ሁኔታ ምንም ይሁን ምን—መልካም አቀባበል የሚደረግበት፣ የሚከበርበት፣ እውቅና የሚሰጥበት፣ ተቀባይነት የሚሰጥበት፣ ደህንነታቸው የተጠበቀ ቦታዎች ናቸው፤ ሆነውም ይቀጥላሉ።
- በፌደራል ህግ መሰረት፣ ሁሉም ልጆች፣ ዜግነታቸው ወይም የመኖሪያ ፈቃድ ሁኔታቸው ምንም ይሁን ምን፣ የኮሌጅ የምክር አገልግሎትን ጨምሮ ከመዋእለ ህጻናት እስከ 12ኛ ክፍል (K-12) ትምህርት የማግኘት መብት አላቸው።
- ትምህርት ቤቶች የወላጅ ፈቃድ ሳይኖር፣ ከተማሪ ፋይል ለፌደራል የኢሚግሬሽን ወኪሎች መረጃ እንዳይሰጡ በጥብቅ የተከለከሉ ናቸው።
- ከዚህ ድረገጽ ይበልጥ ግንዛቤ ማግኘት ይችላሉ፦ www.montgomeryschoolsmd.org/departments/deod/immigration-supports/

እንግሊዝኛ መናገር የማልችል ከሆንኩ ወይም እንዴት መርዳት እንዳለብኝ ሳላውቅ ልጄን በትምህርቱ(ቷ) እንዴት መርዳት እችላለሁ?

- ሁሉም ወላጆች እና አሳዳጊዎች የልጃቸውን ትምህርት መደገፍ ይችላሉ። በማንኛውም ቋንቋ ለመምህሩ ማስታወሻ "ParentVue" ላይ መልክት በማስተላለፍ፣ በኢሜል፣ ወይም ቢሮ በመደወል ከልጅዎ ትምህርት ቤት ጋር መገናኘት ይችላሉ።
- ለአብዛኛዎቹ ጥያቄዎች በተለያዩ ቋንቋዎች መልሶችን ማግኘት ይችላሉ፦ AskMCPS www.montgomeryschoolsmd.org/askmcps-faqs/
- "MCPS Parent Academy" ፓረንት አካደሚ ላይ ነጻ ዎርክሾፕ ትምህርት ይውሰዱ፦ www.montgomeryschoolsmd.org/departments/parentacademy/

የተማሪ አገልግሎት ትምህርት ሰዓቶችን (SSL) እንዴት ማግኘት እና ማቅረብ እችላለሁ?

6ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ላሉ ተማሪዎች በሙሉ አገልግሎት በመስጠት የሥራቸውን የተማሪ አገልግሎት ትምህርት ሰዓት ማቅረብ የስቴት መስፈርት ነው። ተማሪዎች ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለመመረቅ 75 SSL ሰአት ማግኘት አለባቸው፤ ከ 5ኛ ክፍል በኋላ በሠመር ወቅቶች የተማሪ አገልግሎት ሰዓት (SSL) አገልግሎት መጀመር ይችላሉ።

1. ተማሪ ለመቀበል የተፈቀደላቸውን ድርጅቶች ዝርዝር በዚህ በይነመረብ ላይ ይምረጡ፦ bit.ly/SSLOpportunities.
2. ቅጽ ይሙሉ፦ www.montgomeryschoolsmd.org/departments/forms/pdf/560-51.pdf

ልጄ የሚማርበትን/የምትማርበትን ትምህርት ቤት መቀየር እችላለሁ?

በሞንትጎመሪ ካውንቲ ያሉ ተማሪዎች በሚኖሩበት አካባቢ ወይም በግለሰባዊ ሁኔታ የተዘጋጀ ትምህርት ፕሮግራም (IEP) በሚሰጥበት ትምህርት ቤት መከታተል ይጠበቅባቸዋል። ካስፈለገ፣ ቤተሰቦች የትምህርት ቤት ምደባ ለውጥ ለማድረግ (COSA) የተለየ ትምህርት ቤት መጠየቅ ይችላሉ። ነገር ግን ጥያቄ ቢቀርብም የትምህርት ቤት ለውጥ የማድረግ ዋስትና አይሰጥም።

የትምህርት ቤት ዝውውር ጥያቄ ለማቅረብ "ParentVue" ላይ ማመልከት ይችላሉ። ይህን ድረገጽ ይክፈቱ፦ www.montgomeryschoolsmd.org/info/transfers/ for more information

ለልጄ የቤት ስራ እርዳታ እንዴት አገኛለሁ?

እርዳታ ለመጠየቅ ለልጅዎ መምህር ይደውሉ፣ ኢሜይል ይላኩ፣ ወይም ማስታወሻ ይጻፉ። ብዙ ትምህርት ቤቶች የትምህርት ቁሳቁሶች/ሪሶርሶች እና ድጋፍ አላቸው። እንዲሁም ስለ ተጨማሪ የትምህርት መገልገያዎች/ሪሶርሶች ይህን ድረገጽ ይጎብኙ፦ www.montgomeryschoolsmd.org/students/homework

የምሳ ምግብ ዝርዝር የት ማግኘት እችላለሁ?

በእያንዳንዱ ት/ቤት የሚዘጋጀውን የምግብ ዝርዝር እዚህ ማግኘት ይችላሉ፦ schools.mealviewer.com/district/MontgomeryCountyPublicSchools.

ለአብዛኛዎቹ ጥያቄዎች "AskMCPS"
በማንኛውም ቋንቋ መልስ ማግኘት ይችላሉ።

AskMCPS በዚህ ስልክ ቁጥር ይደውሉ 240-740-3000
በዚህ አድራሻ ኢሜል ያድርጉ፦ AskMCPS@mcpsmd.org